# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

7

- ★ ፊት ለፊት የማይጋፈጡትን ከበስተኋላ
- ★ በአብዮቱ ሂደት ላይ የመደቦች መንሸራተትና ትግል
- ★ ወዝ አደሩ ይናገር
- ★ "ምን መደረግ አለበት" ሌኒን
- ★ የታሪክ ቁስ አካልነት

ሐምሌ ፴ - ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# ፊት ለፊት የማይጋፈጡትን ከበስተኋላ

በሰብአዊና በተፈጥሮ ሀብቷ እጅግ የታደለችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ጭቆና ታፍና የተጐሳቆለችና የታረዘች ሀገር ሆና ቆይታለች ። ይቺ ለምለምና ሀብታም አገር ፤ ይቺ በወንዞቿ ፤ በጅረቶቿ ፤ በተራሮቿ በደኖቿ ተወዳዳሪ በማይገኝላት ለም አፈር የታደለች ሀገር እስከዛሬ ተንሰራፍቶባት በቆየው የብዝበዛ ሥርዓት የተነሣ ለብዙኃን ዜጐቿ የረኃብ ፤ የቸነፈር ፤ የስቃይና የበሽታ ምድር ሆና እፍኝ ለማይሞሉ በዝባዦች ደግሞ ምድረ ገነት ሆና ፍርድና ፍትሕ የተጓደለባት የጥቂቶች አገር ሆና ቆይታለች ።

በዚች ሀብታምና ለምለም በሆነች ሀገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያንጠፈጥፈው ላቡ ሊሰጠው የሚችለውን የኑሮ ፍሥሐ ተነፍጐ ከዘመን ዘመን በኑሮ ጠርዝ ላይ ተንጠልጥሎ ሲሰቃይና ሲታገል ብዙ መስዋዕትነትና መከራ የተቀበለበትን አኩሪ ታሪኩን ጽፏል ። በሌላ በኩል ደግሞ የመደብ ጠላቶቹ ለእብሪታቸውና ለግፈኛነታቸው ምንም ዓይነት ወሰን ሳያውቁለት ይህን ታጋይና ኩሩ ሕዝብ በረኃብ አለንጋ ፤ በበሽታ ፤ በድንቁርና አስረው ምን ያህል ያሰቃዩት እንደነበረ ሌላው ቢቀር የወሎው እልቂት ገና ለብዙ ትውልዶች የኢትዮጵያ ፊውዳል ሥርዓት በጭቁኑ ሕዝብ ላይ ለፈጸመው በደል «አቤት» እንዳለ የሚኖር ምስክር ነው ።

በዚህ ሁሉ ግፍና መከራ እየተቀሰቀሰ ለዘመናት የተጠራቀመው የሕዝብ ቁጣና ትግል በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ፈነዳ ። ሀገራችን ጨርሳ አይታ በማታውቀው አብዮታዊ ማዕበል ተጥለቀለቀች። እንደሰደድ እሳት ከዳር እስከዳር የተቀሰቀሰው ትግል በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ተጠራቅመው የሚጨፍሩትን ጭቆናዎች በየመልካቸው ለመቋቋምና ለመደምሰስ ከየአቅጣጫውና በየአቅጣጫው የሚደረግ ሕዝባዊ ትግል በመሆኑ የአድኃሪዎች ተንኰል ፤ ሤራ ፤ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካና ልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ መፍጨርጨር ይህንን አብዮታዊ ማዕበል ሊቋቋመው አልቻለም ።

የኢትዮጵያ ጭቁኖች በአብዮታዊው የትግል ጐዳናቸው ላይ ደመኛ ጠላቶቻቸው የሚጋርጡባቸውን ልዩ ልዩ እንቅፋቶች ተራ በተራ እየተወጡ በትግልና በመስዋዕትነት እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ድሎችን ተጐናጽፈዋል ።

መስከረም ሁለት ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ለዘመናት የኢትዮጵያ ጭቁኖች የተጫነባቸው የጭቆና ቀንበር ቁንጮና ምልክት ሆኖ የቆየው የዘውድ አገዛዝ ተገርስሶ ተጣለ ። በዚህም አዲስ የድልና የትግል ምዕራፍ የከፈተው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ትግሉን እያፋፋመ ገስግሶ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ኅብረተሰባዊነት የአብዮታችን መመሪያ መሆኑ ታወጀ ። ከዚሁም ተከታትሎ የኢትዮጵያ ወጣቶች ከገበሬው ተዋህደው ጭቁኑን ገበሬ አንቅተውና አደራጅተው የትግሉ ሙሉ ተሳታፊ ለማድረግ እንዲችሉ ለብዙ ዘመናት ተራማጆች ተሰልፈው የታገሉበት «ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ከሠራተኛው ተዋሃድ» የሚለውን ጥሪ ከሥራ ላይ ለማዋል የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ታወጀ ። ወጣቱ በታላቅ አብዮታዊ መንፈስ ወደ ገጠር በመሠማራት ሰፊውን ገበሬ ማንቃትና ማደራጀት ጀመረ ።

የአብዮቱ የማያወላውል ግስጋሴ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶች ቅስም እየሰበረ በመግፋቱ የካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በአረመኔው የፊውዳል አገዛዝ ስር ተራማጆች በሙሉና ጭቁን ገበሬዎች ደማቸውን እያፈሰሱ የታገሉትና ያጋለጡት የመሬት ስሪት ፈርሶ በነዚሁ ወገኖቻችን ደም የተጻፈው «መሬት ላራሹ» የሚለውን አብዮታዊ መፈክር የሚያጸድቅ አዋጅ ወጣ ። የዘመናት ትግልና መስዋዕትነት በሰጠው በዚህ አብዮታዊ ፍሬ የበዝባዦች ቅስም እንደገና ቢሰበርም የጭቁኖች ደስ



ታና የትግል ወኔ የዚያኑ ያህል ተበራታ ። የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከዳር እስከ ዳር ሰልፍ በመውጣት በዚህ አብዮታዊ ትግላቸው ባስገኘላቸው ድል መደሰታቸውን ብቻ ሳይሆን ይህ አዋጅ ሙሉ በሙሉ ከሥራ ላይ እንዲውል ከሚፈለግባቸው ትግልና ታታሪነት ፈጽሞ ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን ማየት ለሚሹ ሁሉ አሳዩ ።

የኢትዮጵያን ፊውዳል ሥርዓት ከሥረ መሠረቱ እናግቶ ፤ ሕዝቡን በአብዮታዊ የትግል መንፈስ ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሶ በሀገራችን የሚካሄደውን የመደቦች ትግል እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ያደረሰው ይህ አዋጅ ሕዝብና ታሪክ ተፍቷቸው ያለፉትን አድኃሪዎች ይህንን ታጋይና ቆራጥ አብዮታዊ ሕዝብ ካሁን ወዲያ ፊት ለፊት ገጥመው እንደማያሸንፉት አስገነዘባቸው ። የሕዝብ የደስታ ስሜት ብቻ ሳይሆን ለመጭው ትግል ያለውን ቆራጥነትና ዝግጁነት የተመለከቱ አድኃሪዎች ታክቲክ ለመለወጥ ተገደዱ ። ፊት ለፊት መቋቋም ያልቻሉትን አብዮት በስተጀርባ ለመውጋት የተንኮል ፤ የሤራ ፤ የአሻጥር ትግላቸው መጠን በሳተ ሁኔታ እንዲፋፋም አደረጉት ።

ከዚህን ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ አብዮት እየገፋ አዳዲስ የድል ምዕራፎች እየከፈተ ሲሄድ ተስፋ የቆረጡ አድኃሪዎች ፤ ፊት ለፊት መግጠም ያልቻሉት አድኃሪዎች የአሻጥር ትግላቸውን በዚያው ልክ አፋፋሙት ። የሕዝቡ ትግል እነሱንም አስተምሯቸዋልና የነቁ አድኃሪያን እንደ እንጉዳይ በያለበት ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ ።

ለመሆኑ የዚህ አሻጥር ይዘት ምንድን ነው ? በመሠረቱ የሕዝብ አብዮታዊ ክንድ ተጭኖ ያስደነገጣቸው አድኃሪያን እያለቁና እየደቀቁ መሄዳቸው ሲሰማቸው የበስተጀርባ ትግላቸውን የሚያፋፍሙት በሁለት የተቀነባበሩ አቅጣጫዎች ነው ።

የኢኮኖሚ አሻጥር አለ ። የፖለቲካ አሻጥር አለ ። የኢኮኖሚው አሻጥር ዋና ዓላማው ምርት እንዲወድቅ ፤ የዕቃ እጥረት በተለይም ሰፊው ሕዝብ ለዕለታዊ ኑሮ የሚፈልጋቸው ዕቃዎች ከገበያ እንዲጠፉ ወይም ዋጋቸው ወደሰማይ እየናረ ሰፊው ሕዝብ እንዳይደርስባቸው በማድረግ ችግሩን ማባባስ ፤ ሕዝቡን ማስቆጣት ፤ ማበሳጨት ፤ የቀድሞውን አድኃሪ ሥርዓት ፤ ያንን አዋርዶና ረግጦ ይዞት የነበረውን ፤ ያንን በመቶ ሺህ እየተቆጠሩ በረኃብና በቸነፈር እንዲረግፉ ያደረጋቸውን በክት ሥርዓት እንዲናፍቅ ፤ በዚህም ጭቁኖች በራሳቸው አብዮት ላይ ክንዳቸውን አንሥተው ከፀረ—አብዮት ደመኞቻቸው ጋር እንዲተባበሩ ይሞክራል ።

<u>በወልቂጤ</u> ፤ <u>በአሩሲ</u> ፤ <u>በባሌ</u> ፤ በሌሎችም ቦታዎች የተመለከትናቸው አሻጥሮች የዚህ ፀረ—አብዮት ዘዴ ዋና ምስክሮች ሆነው ለታሪክ የሚተላለፉ ናቸው ።

ሌላው ደግሞ የፖለቲካ አሻጥር ነው ። ሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት እንዳያገኝ ፤ ነቅቶም እንዳይደራጅና ለሥልጣን እንዳይበቃ ማኅበሮቹን እንዳያቋቁም ሌት ተቀን በአሻጥር ይመቱታል ። የውይይት ክበቦችን እንዳይመሠርት ይታገሉታል ። አታንብ ፤ አትጠይቅ ፤ ግን «ታገል» ይሉታል ። ይህ ሁሉ የተቀነባበረ ሤራ ሰፊው ሕዝብ ነቅቶ ፤ ተደራጅቶና ታጥቆ ለሥልጣን እንዳይበቃ ነው ።

በመሠረቱ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስና አዲስ ኑሮ ለመጀመር ተነሣሥቶ ሲታገል እንደዚህ ዓይነቱ አሻጥር ያልተሰነዘረበት ነፃ ሕዝብ በየትም አይገኝም ። በሶቪየት ኅብረት ፤ በቻይና ፤ በቪዬትናም ፤ በኩባ ፤ በኮርያ ፤ በጠቅላላው ዛሬ ደመኛ ጠላቶቻቸውን ደምስሰው አዲስ ኑሮ በመገንባት ላይ ያሉ አገሮች ሁሉ ከግባቸው የደረሱት መሥዋዕትነት በተሞላው ታላቅ ተጋድሎ ከፊት ለፊት የሚመጡባቸውን ጠላቶች ብቻ ሳይሆን መስለው ተደባልቀው ከጀርባቸው ከሚያሴሩባቸው ፤ ለመገንባት የሚፈልጉትን አዲስ ኤኮኖሚ ከሚያዝረከርኩባቸው ፤ ስርጎ ገብ የውስጥ አርበኞች ጋር እጅግ የተወሳሰበ ትግል ማካሔድ በመቻላቸው ነው ።

እነዚህ ሕዝቦች አብዮታቸውን በሚያካሔዱበት ጊዜ በስተጀርባ የመጡባቸው ጠላቶች አስርበውና አራቁተው ሊያዳክሟቸው ፤ ሊከፋፍሏቸው ያልፈጸሙባቸው አሻጥር አልነበረም ። ነገር ግን

እነዚህ የነቁ ፤ የተደራጁና የታጠቁ ታጋይ ሕዝቦች አድኃሪ ኃይሎች ኢኮኖሚያቸውን አዝረክርከው የጫኑባቸውን ረኃብና መራቆት ያው የመደቦች ትግል አካል አድርገው ተርበውና ተራቁተው አብዮታቸውን ገቱበት እንጂ በዚህ ሴራ ትግላቸውን ፈትተው አብዮታቸውን አላስቀለበሱም ።

ጥያቄው ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚለው ነው ። መልሱም ቀላል ነው ። እነዚህ ታጋይ ሕዝቦች አብዮቱን በሚያካሔዱበት ጊዜ ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ደረጃ ላይ ነበሩ ። በትግላቸው ውስጥ ቢራቡ ፤ ቢጠሙ ፤ ቢራቆቱ ፤ ቢታረዙ ይህ ራሱ የጠላት መደቦች የሚጠቀሙበት የትግል ዘዴ ያመጣው ችግር መሆኑ ይገባቸው ነበር ። ከሁሉም በላይ የሚያነቃ ፤ የሚያደራጅና የሚያስታጥቅ የወዝ አደር ፓርቲ ነበራቸው ። ስለሆነም ጠላቶቻቸው በስተጀርባ በሚያውጠነጥኑት አሻጥር የሚመጣባቸውን ረኃብና ቸነፈር መቋቋምና አብዮቱን ወደፊት ማራመድ ራሱ የመደቦች ትግል ማካሔድ እንደነበረ ያውቁ ነበር ።

እነዚህ ታጋይ ሕዝቦች ከፍተኛ የንቃት ደረጃ ላይ ስለነበሩ በአብዮት ጊዜ ጠላቶቻቸው እያባባሱ በሚጭኑባቸው ችግር የተነሣ መልሰው የቀድሞውን ሥርዓት አልናፈቁም ። በአብዮታቸው ላይ ከጠላቶቻቸው ጋር ተባብረው አልተነሱም ። ጊዜያዊ የሆነ ችግርን በመራራ ትግልና በመስዋዕትነት ተወጥተው አዲስ ኑሮዋቸውን መገንባት የሚጀምሩት ጠላቶቻቸው ሰርገው ገብተው እንደሚገፋፏቸው በአብዮቱ ላይ በመነሳት ሳይሆን አብዮቱን ከግቡ በማድረስ መሆኑን ስለተገነዘቡ የጠላቶቻቸው የኢኮኖሚ አሻጥር ትጥቃቸውን አላስፈታቸውም ።

በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለው የተፋፋመ የመደቦች ትግል በጭቁን ሕዝቦች ድል የሚፈጸመው የኢትዮጵያ ሕዝቦች በኢኮኖሚያቸው ላይ የሚደረገውን አሻጥር የመደቦች ትግል አንዱ መልኩ መሆኑን ተገንዝበው በዚህ በኩልም የሚፈታተኑዋቸውን ጠላቶቻቸውን ሞቋቋም ሲችሉ ነው። አድኃሪ ኃይሎች ራሳቸው የሚቀሰቅሱትን የኢኮኖሚ ቀውስ በሌላ በኩል ዘወር ብለው አብዮቱ በሕዝቡ ላይ ያወረደው መዓት አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። በሌላ አንፃር ደግሞ አናርኪስቶችና ከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች ወዳጅ መስለው በመደባለቅ ወዝአደሩ ነቅቶ ይህንን አሻጥር እንዲቋቋምና ስንት ትምህርትና ንቃት መቅሰም የሚገባውን ሕዝብ « ነቅተሃል በቅተሃል » እያሉ እንዳይወያይ ፤ እንዳይማር ፤ እንዳይነቃ ታላቅ የፖለቲካ አሻጥር ይፈጽሙበታል ። ስለሆነም እነዚህ ከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች በሌሎች አገር ጭቁን ሕዝቦች የኢኮኖሚ አሻጥርን ተቋቁመው አብዮታቸውን ከግቡ ያደረሱት ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት አግኝተው መሆኑን ስለሚያውቁ ለቅልበሳ ሴራቸው ሲሉ ወዝ አደሩ እንዳይነቃ መሞከራቸው ፈጽሞ የሚያስገርም አይደለም ።

ነገር ግን በተቀነባበረ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አሻጥር የኢትዮጵያን ጭቁኖች አብዮት እንገታለን ወይም እንቀለብሳለን ብሎ ማሰብ ካሁን ወዲያ ከንቱ ህልም እንደሆነ አድኃሪዎች ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል ። የኢትዮጵያ አብዮት ህልውናውን ለመጠበቅ ትግሉን በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው መስክ በሚያካሄዱት ፀረ—አብዮት ኃይሎች ላይ የማያወላውል ክንዱን ያነሳባቸዋል ። የሕዝቡን አብዮታዊ ትግል አዝረክርከው በሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ቀውስ ጭቁኑን በጭቁን ላይ ለማስነሳትና ሀገራችንንና አብዮታችንን ለፀረ—አብዮት ሴራቸው ለማመቻቸት የሚሞክሩ የቀድሞው ሥርዓት ርዝራዦች ፤ ኢምፔሪያሊስቶችና ከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች የኢትዮጵያን አብዮት ካሁን ወዲያ ምንም ዓይነት መፍጨርጨር ሊገታው እንደማይቻል መገንዘብ አለባቸው ። በየጊዜው የሚጠነስሱትን ፀረ—ሕዝብ ሴራ በየጊዜው የተባበረው የሰፊው ሕዝብ ክንድ እያደቀቀው አብዮቱ ወደፊት ይገሰግሳል።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ »